STREAM ACCELERATOR

ስትሪም አክስለሬተር ፡ የውሃና ንፅህና ዘርፍ ኢንቨስትመንት  ማነሳሻ

አይስአዲስ ከAqua for All እና Fair & Sustainable ጋር በመተባበር የሚተገበረው ስትሪም አክስለሬተር መርሃ ግብር እምቅ አቅም ያላቸውን አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞችን ኢላማ ያደረገ ሲሆን፣ ልዩ ልዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን እና የቴክኒክ ድጋፍን ይሰጣል። ይህ ውጥን በኢትዮጵያ በውሃና ንፅህና ዘርፍ ውስጥ ያሉ ኢንተርፐራይዞች የሚገጥሟቸውን የካፒታል ክፍተቶች በማጥበብ የንግድ ሥራ ሞዴሎቻቸውን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ያለመ ነው።

የመርሃ ግብሩ አላማዎች

ስትሪም አክስለሬተር በኢትዮጵያ የዳበረና በግል ዘርፉ የሚመራ የውሃና ንፅህና ዘርፍ የማጎልበትን ዓላማ አንግቦ የሚሰራ ውጥን ነው።

መርሃ ግብሩ የውሃና ንፅህና መጠበቂያ ኢንተርፐራይዞች ስራቸውን እንዲያሳድጉ፣ አዳዲስ ገበያዎች ውስጥ እንዲገቡ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት እንዲችሉ የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። በመሆኑም በዕውቀት መጋራት እና በአቅም ግንባታ መርሆቹ፣ ውጥኑ በዘርፉ ዘላቂ እድገትና ፈጠራን ለማምጣት ያለመ ነው።

የመርሃ ግብሩ ዋና ዋና ክፍሎች፦

1) የሚመለከታቸውን የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎችን መለየት፡- ስትሪም አክስለሬተር በውሃና ንፅህና ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞችንና እነዚህን ኢንተርፐራይዞችን ለመደገፍ ፍላጎት ያላቸውን የፋይናንስ ተቋማት በማገናኘት፤ ኢንተርፐራይዞቹ በፍላጎታቸው መሰረት የተበጁ የፋይናንስ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይረዳል።

2) የምርት ግምገማ በማድረግ ከፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት  ጋር ማገናኘት፡- መርሃ ግብሩ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች ተስማሚ የፋይናንስ አማራጮችን ለማስገኘት፤ በፋይናንስ አገልግሎቶች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት አካሂዶ ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር ያገናኛል። ይህ እርምጃ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች እድገታቸውን እና የማስፋፊያ እቅዶቻቸውን የሚደግፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ያግዛቸዋል። በተጨማሪም የፋይናንስ ስምምነቶችን የማግኘት ሂደትን ለማቃለል፤ በውሃና ንፅህና ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩ ኢንተርፐራይዞች እና የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት በማመቻቸት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ይሰጣል።

3) በተበጀ ንግድ ሥራ አማካኝነት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፡- መርሃ ግብሩ የአቅም ግንባታ እና ክህሎትን ማጎልበት ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች ያለውን ጠቀሜታ እውቅና በመስጠት፤ ለተሳታፊ ኢንተርፐራይዞች የተዘጋጀ የንግድ ሥራ ድጋፍን ያበረክታል። በመሆኑም የምክር አገልግሎት እና የአንድ ለአንድ የማማከር ክፍለ ጊዜዎችን በማቅረብ፤ የኢንተርፐራይዞቹን የንግድ ክህሎት፣ የአሰራር ቅልጥፍና እና የገበያ ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል ይሰራል። በነዚህ አገልግሎቶች አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች መሰናክሎችን ለመወጣት፣ እድሎችን ለመጠቀም እና በውሃና ንፅህና ዘርፍ ውስጥ ስኬታማ ለመሆን ጠቃሚ ግብዓቶችን ያገኛሉ።

ለተጨማሪ መረጃ http://iceaddis.com/streamን ይጎብኙ።